# የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን

# መመሪያ ቁጥር 111/2008

ህዳር 2008

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

<u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር  111/2008</u>

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን በአዋጁ ከተደነገጉ መርሆዎችና ዘዴዎች ጋር በማጣጣም ለማስፈፀም በማስፈለጉ፣

የዋጋ አተማመን በተሻለ ደረጃ ዘመናዊ፣ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በወጥነት ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የባለስልጣኑ የሥራ ክፍሎች፣ ቅ/ጽ/ቤቶች እና የጉምሩክ ኦፊሰሮች ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወሰን በማስፈለጉ፣

አስመጪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በዋጋ አተማመን ረገድ የሚኖራቸውን መብትና የተጣለባቸውን ግዴታ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 89(4) ስለዋጋ መተመኛ ዘዴዎች እና የዋጋ አተማመን ስርዓት አፈጻጸም በመመሪያ እንዲወሰን እና በአንቀጽ 180(2) ባለስልጣኑ የአፈጻጸም መመሪያ እንዲያወጣ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይኸንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ **የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር** 111/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"ገቢ ዕቃ"** ማለት ወደ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የሚገባ ማንኛውም ዕቃ ማለት ሲሆን ገንዘብን አይጨምርም፡፡
   2) **"ያገለገለ ዕቃ"** ማለት ዕቃው ከተመረተበት የምርት ዘመን በኋላ በጥቅም ላይ የቆየ ዕቃ ሲሆን ያገለገለ ልብስን አይጨምርም፡፡
   3) **"እርጅና ቅናሽ"** ማለት በተሽከርካሪው የኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ የአገልግሎት ዘመንን መሰረት በማድረግ በመቶኛ የሚደረግ ቅናሽ ሲሆን በሌሎች ዕቃዎች ላይ ወጥ የሆነ የመቶኛ ቅናሽ ነው፡፡
   4) **"የጉምሩክ ዋጋ (Customs Value)"** ማለት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሲሆን በጉምሩክ አዋጅ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት የዋጋ አተማመን ዘዴዎች አማካኝነት የሚሰላ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ወይም መውጫ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋና ሌሎች ወጪዎችና ክፍያዎች ጠቅላላ ድምር ወጪ ነው፡፡

5) **"የማነፃፀሪያ ዋጋ** (Reference Value)" ማለት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበውን የዕቃ ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራት እና ለመወሰን የሚያገለግል በጉምሩክ ዳታ ቤዝ ዉስጥ ያለ እንዲሁም በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኘ ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ ፣በወጪ ስሌት እና በዓለም አቀፍ የዋጋ መረጃን መሰረት በማድረግ የተገኘ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች ዋጋ መረጃ ነው፡፡

6) **"መነሻ ዋጋ** (*Minimum Value*" ማለት የዕቃውን ዋጋ አሳንሶ የማቅረብ ድርጊቶችን ለመከላከል ሲባል በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ከፍተኛ ሥጋትና ተደጋጋሚ ችግር ባለባቸው የተወሰኑ ዕቃዎች ላይ በጉምሩክ የሚደራጅ የዋጋ መረጃ ነው፡፡

7) **"የ ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ (FOB Price) ማለት"** የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ የመጨረሻ መጫኛ ቦታ (ወደብ) ድረስ ለዕቃው የተከፈለ/የሚከፈል ወጪ ድምር ሲሆን አንዱ የዓለማቀፍ የንግድ ስምምነት ዓይነት (INCOTERM) ነው፡፡

8) **"የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ (CIF price) ማለት"** የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ የመጨረሻ መጫኛ ቦታ (ወደብ) ድረስ ለዕቃው የተከፈለ/የሚከፈል ወጪ እና ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የኢንሹራንስ፣ የማጓጓዣ፣ የማስጫኛ፣ የማውረጃ እና የመንከባከቢያ ወጪ ድምር ሲሆን አንዱ የዓለማቀፍ የንግድ ስምምነት ዓይነት *(INCOTERM)* ነው፡፡

9) **"የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት** *(Ethiopian Customs Valuation System[ECVS])"* **ማለት** በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ወይም ወጪ እቃዎች ዋጋ መረጃን እና የዓለማቀፍ ዕቃዎች ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ዳታቤዝ ነው፡፡

10) **"በአንድ ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች"** ማለት በአንድ ሉአላዊት ሀገር የተመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን፣ በተፈጥሮ የተገኙ ወይም በቁፋሮ የተገኙ እቃዎችን ይጨምራል፡፡

11) **"በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገሮች"** ማለት በአለም አቀፍ የንግድ ድርጅት (WTO) ወይም በተባበሩት መንግስታት (UN) የአገሮች የእድገት ደረጃ ዝርዝር መሰረት በተመሳሳይ ዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገራት ሲሆኑ የአህጉራዊ ነባራዊ ሁኔታም ከግንዛቤ የሚያስገባን የአገራት ዝርዝርን ይጨምራል፡፡

12) **"ተቀራራቢ ዕቃ"** ማለት በአንድ አይነት ኢንዱስትሪ ወይም በአንድ አይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱ ዕቃዎች ማለት ሲሆን፣ የአንድ ዓይነት እቃዎችና ተመሳሳይ ዕቃዎችን ይጨምራል፡፡

*13)* **"በአገር ውስጥ ገበያ ነጠላ መሸጫ ዋጋ (Domestic Market Selling Unit Price)"** ማለት ወደ አገር ውሰጥ የገባው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገቡና በገቡበት ሁኔታ በከፍተኛ ብዛት የተሸጠበት (የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ሳይጨምር) ነጠላ ዋጋ መረጃ ማለት *ነዉ፡፡*

14) **“የጉምሩክ ዋጋ ማጣራት”** ማለት በሚመለከታቸው የጉምሩክ ኦፊሰሮች አማካኝነት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር የተደረገው የዕቃዎች ዋጋ ትክክለኛ የጉምሩክ ዋጋ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ወይም ለማጣራት ይቻል ዘንድ ለዋጋው ወይም ለስሌቱ መነሻ የሚሆኑ ሰነዶችን የመመርመር ሂደት ሲሆን፣ የመጀመሪያ የዋጋ ማጣራት፣ በድኅሚ የማጣራት እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በትክክል እስከሚሰላ ድረስ የሚደረገውን የዋጋ ማጣራት ሂደት ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

15) **“ዋጋ የመወሰን ስልጣን ማለት”** በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከዋጋ ትመና ጋር በተያያዘ ስለፈጸማቸው ጥፋቶች ወይም ልዩነት ስለመገኘታቸው በዋጋ አጣሪ ኦፊሰሮች አማካኝነት ዋጋ የማጣራት፣ የማስተካከል ወይም ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሂደት ነው፡፡

16) **“የጉምሩክ ዋጋ ውሳኔ ክለሳ (Review)”** ማለት በሥራ ኃላፊነት መሠረት በአንድ ኦፊሰር የተሰጠ የዋጋ ትመና ውሳኔ በስራ ላይ ካላው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አንጻር ስላለው ትክክለኛነት ቢያንስ በአንድ ደረጃ በበላይ ኦፊሰሮች ወይም በክለሳ ኮሚቴ አማካኝነት የሚተገበር በድኅሚ የማጣራት ሂደት ነው፡፡

17) **“የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ (Valuation Details Declaration,VDD)”** ማለት ከዕቃ ዲክሌራሲዮን በተጨማሪ የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በመሙላት ለባለስልጣኑ በዝርዝር የሚያሳውቅበት በባለሥልጣኑ የተዘረጋ ሥርዓት ወይም የተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሳወቂያ ሥነ-ሥርዓት ሲሆን፣ በወረቀት መልክ የሚዘጋጅ ቅጽንም ይጨምራል፡፡

18) **“ዳይሬክቶሬት”** ማለት የዋጋ ትመና እና የታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

19) **“ባለሥልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

20) **“አዋጅ”** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

21) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላት እና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ

1) ቀረጥና ታክስ በሚከፈልባቸው ወይም በማይከፈልባቸው ገቢ ወይም ወጪ ዕቃዎች፣
2) ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር ከተለቀቁ በኃላ በድኅሚ ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም፣
3) የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኂላ ኦዲት የሚካሄድባቸው ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም፣

4) የእርጅና ቅናሽ ስሌት አሰራር ሳይጨምር ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እና በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ጉምሩክ ዋጋ አወሳሰን ሁኔታ

## ምዕራፍ አንድ

## የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ዘዴዎች አፈፃፀም

4. **መርህ**

የዕቃዎች የጉምሩክ ዋጋ በሚወሰንበት ወቅት የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ፣ የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴ፣ የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴ፣ ወደ ኋላ የማስላት አተማመን ዘዴ፣ በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ አተማመን ዘዴ እና ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ በቅደም ተከተል በመጠቀም ይሆናል፡፡

5. **የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ አፈፃፀም**

1) ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ እቃ የግብይት ዋጋ ተደርጐ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የግብይት ዋጋ ሲሆን በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች ታክለውበት ነው፡፡

2) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ *(Declared Value)* በቀጥታ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 90(1)(ሀ)-(መ) የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ እና/ወይም የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ አለ ብሎ ሲያምን ወይም ሲገምት ነው፡-

ሀ/ በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የዕቃው መግለጫዎች ፣ የብዛት፣ የምርት-ሀገር፣ የምርት ዘመን መግለጫዎች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች በትክክል ካልተገለጹ ወይም ካልቀረቡ፣

ለ/ በሀሰት ወይም በተጨበረበረ መልኩ የተዘጋጀ ሰነድ/ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ካለው፣

ሐ/ በአዋጁ አንቀፅ 96 ላይ የተጠቀሱት ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ ካልተካተቱ ወይም ዋጋቸውን ለመተመን የሚያስችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢው ካላቀረበ፣

መ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የእያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ውስጥ የሚገኙ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነት በማነስ ከ10% በላይ ከሆነ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲከሰቱ የሚከተሉት ተግባራት በቅደም ተከተል ይፈፀማሉ፡-

ሀ/ የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ የዲክላራሲዮን አቅራቢውን ዋጋ የጠረጠረበትን ምክንያት በመግለጽ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም ስለ ዕቃው ዋጋ ትክክለኛነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ 1 መሰረት ሞልቶ እንዲያቀርብ ይጠይቃል፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2(መ) የተመለከተው ሲያጋጥም በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበው የዕቃው ዋጋ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለዉ የቀረበው ዋጋ በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ 2 መሰረት ለባለስልጣኑ ማቅረብና ማስረዳት ከቻለ እና በሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ሲፈቀድ ነው፡፡

ሐ/ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የተጠየቀውን ማስረጃዎች በዚህ ንዕስ አንቀፅ (ሀ) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ ካላቀረበ ወይም ያቀረበው ማስረጃ የዋጋ ትመና ኦፊሰሩን ጥርጣሬ ሊያስወግድ ካልቻለ የዋጋ ትመና ኦፊሰሩ ጥርጣሬውን ያላስወገደበትን ምክንያት በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ 3 ላይ በግልጽ በማስቀመጥ እና ለዲክላራሲዮን አቅራቢው ማስረጃውን ባቀረበ በአንድ የስራ ቀን ውስጥ በማሳወቅ ወደሚቀጥለው የዋጋ አተማመን ዘዴ ይሸጋገራል፡፡

## 6. <u>በገዥና ሻጭ መካከል ግንኙነት አለ ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ስለሚኖር አሰራር</u>

1) ቅ/ጽ/ቤቱ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከሻጭ ጋር ግንኙነት አለው ብሎ ከጠረጠረ ወይም ግንኙነቱ በግብይት ዋጋ ላይ ተጽእኖ ስለማሳደሩ ከጠረጠረ በልዩነት ለሚፈለገው የቀረጥና ታክስ መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 41/2/ በተደነገገው መሰረት ዋስትና በመያዝ ለጊዜው በማስተናገድ ቀጣይ ማጣራት እንዲደረግ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መጠይቅ ወይም ቅጽ ላይ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን በማስሞላት ዝርዝር ሪፖርት ከአስፈላጊው ደጋፊ ሠነዶችና ማስረጃዎች ጋር በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለዳይሬክቶሬቱ መላክ አለበት፣

2) ዳይሬክቶሬቱ ሪፖርትን መነሻ በማድረግ ግኑኝነት ያላቸው መሆኑን ካላመነ የደረሰበትን ውጤት ለሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርቱ በደረሰው በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

3) ዳይሬክቶሬቱ የደረሰበት ውጤት በገዥና ሻጭ መካከል ግንኙነት እንዳለ የሚያሳይ ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ቀጣይ የማጣራት ሂደቶች ያከናውናል፡፡

7. <u>ግንኙነት ያላቸው አካላት ዋጋ ማጣራት ሂደት</u>

1) በገዢና ሻጭ ግንኙነት ሲኖር ዲክላራሲዮን አቅራቢው በባለስልጣኑ በተዘጋጀው መጠይቅ ወይም ቅጽ በአግባቡ ሞልቶ ከሚያቀርበው መረጃ እና ቅ/ጽ/ቤቱ ከላከው ሪፖርት በመነሣት ዳይሬክቶሬቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ያጣራል፤

   ሀ/ የዕቃው ዋጋ የተወሰነበት ሁኔታ በተለይ ዕቃውን በሚያመርተው የኢንዱስትሪ ዘርፍ በማንኛውም ነፃ የውድድር ገበያ ሁኔታ ትክክለኛ ዋጋ በሚወሰንበት ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን፣

   ለ/ ዋጋው የተወሰነው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሌሎች ገዢዎች በተወሰነበት ሁኔታ መሆኑን፣

   ሐ/ የግብይት ዋጋው አጠቃላይ ዕቃውን ለማምረት የሚያስወጣውን ወጪ እና አምራቹ በተመሳሳይ ወቅት ተመሳሳይ ዕቃ በመሸጥ ከሚያገኘው ትርፍ ጋር የሚመጣጠን ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን ናቸው፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት ግንኙነት ባላቸው አካላት መካከል በተደረገ ግብይት የቀረበው የዕቃው ዋጋ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

   ሀ/ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያለመኖራቸውን የጉምሩክ አፈሰሩ ካረጋገጠ፣ ወይም

   ለ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10% የበለጠ ከሆነ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያቀረበው ዋጋ ሌሎች በዲክላራሲዮን አቅራቢዉዎች ከገዙበት ተቀራራቢ እና ትክክለኛ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ማስረዳት ከቻለ፣ ወይም

   ሐ/ ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ከተወሰነ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10% ያልበለጠ ከሆነ ፣ ወይም

   መ/ በወጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ የማስላት ዘዴ ከተወሰነ አንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ጋር ያለው ልዩነት በማነስ ከ10% ያልበለጠ ከሆነ፣

   ሠ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ በተመሳሳይ ወቅት ወደ ኋላ በማስላት ወይም በወጪ ስሌት ዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት ከተወሰነ የዕቃ ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10% የበለጠ ቢሆንም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያቀረበው ዋጋ ሌሎች ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ከገዙበት ዋጋ ጋር ተቀራራቢ እና ትክክለኛ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ማስረዳት ከቻለ፣

ረ/ ከፊደል ተራ ቁጥር "ለ" እስከ "ሠ" የተጠቀሱት ማነፃፀሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ የንግድ ደረጃ ልዩነት፣ የብዛት ልዩነት፣ በአዋጅ አንቀጽ 96 መሠረት በዋጋ ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች እና ሻጩ ከገዥው ጋር ባልተዛመዱበት ሁኔታ ያወጣቸው ወጪዎች እና ሻጩ ከገዥው ጋር በተዛመድበት ሁኔታ ደግሞ እነዚህ ወጪዎች በሻጩ ያልተከፈሉ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት የሚኖርበት ሲሆን የተጠቀሱት ማነፃፀሪያዎች በዲክላራሲዮን አቅራቢው አነሳሽነት በጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናሉ፡፡

3) ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ያደረገዉ የማጣራት ሂደት ዉጤት በተመለከተ ለቅ/ጽ/ቤቱና ለዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ በጹሁፍ ከማሳወቁ በተጨማሪ በECVS ሲስተም ዉስጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀዉ ፎርማት መሰረት መረጃዉን እንዲሞላ ያደርጋል፤፤

4) ቅ/ጽ/ቤቱ በግንኙነት ያላቸው አካላት አስመልክቶ የተሰጠው የዋጋ ውሳኔ እና በሲስተሙ ውስጥ የተመዘገበው መረጃ መነሻ በማድረግ ዲክላራሲዮን አቅራቢው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ እቃው ከሻጩ ሲያመጣ ሌላ የተለየ ሁኔታ ወይም መረጃ እስካልተገኘ ድረስ በዚሁ መሠረት ተመሳሳይ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. <u>የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም፡-</u>

1) የዕቃውን ዋጋ በግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 91 በተደነገገው መሠረት ዕቃው ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩና ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጡ የአንድ አይነት ዕቃዎች አስመልክቶ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት፡-

ሀ/ ተመሣሣይ ንግድ ደረጃ ኖሯቸው ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

ለ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

ሐ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ለተጠቀሱት ማስተካከያው ሲደረግ በተጨማሪ የግብይት ዋጋው በአዋጅ አንቀጽ 96/1/ የተጠቀሱት ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዝ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች

እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓዣ ፣ የመጫን፣የማውረድ የአያያዝ የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ባለስልጣኑ የዋጋ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በዲክላራሲዮን አቅራቢ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች መረጃ ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፣

5) ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር ያደረገው የአንድ አይነት ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ በባለሥልጣኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ከሚገኘው የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋን በማነፃፀር ይወስናል፡፡

## 9. የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን ዘዴ አፈጻጸም

1) የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 8 መሰረት ሊወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ያደረገው ዕቃ ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩ ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጡ የተመሳሳይ ዕቃዎችን አስመልክቶ ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀፅ 92 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት፡-

ሀ/ ተመሣሣይ ንግድ ደረጃ ኖሯቸው ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

ለ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

ሐ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ ተመሣሣይ ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተመሣሣይ ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡

3) በአንቀጽ 2 ላይ ለተጠቀሱት ማስተካከያውን ሲደረግ በተጨማሪ የግብይት ዋጋው በአዋጅ አንቀጽ 96/1/ የተጠቀሱት ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዝ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ የአያያዝ የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 በተገለጸው መሰረት ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ባለሥልጣኑ የዋጋ ውሳኔ ሲያስተላልፍ በዲክላራሲዮን አቅራቢ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች መረጃ ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡

5) ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር ያደረገው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ በባለሥልጣኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ከሚገኘው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በማነፃፀር የሚወስን ነዉ፡፡

10. <u>ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ አፈጻጸም</u>

1) የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣8 እና 9 መሰረት ሊወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 93 በተደነገገው መሠረት የዕቃዎችን ዋጋ ለማስላት ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በተደረገ ግብይት በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ወይም በሌሎች ዲክላራሲዮን አቅራቢዉዎች እቃው ከተጫነበት አገር በቀጥታ ወይም ከሌላ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወይም ወደ አገር ውስጥ ከገባ 90 ቀናት ያልበለጠው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጡበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመስረት እና በአዋጁ የተጠቀሱት ዝርዝር ወጪዎችና የትርፍ መጠን ከመሸጫ ዋጋው በመቀነስ ይወሰናል፡፡
2) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል ሻጭ ማለት ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ሲሆን ገዥው ማለት ዕቃውን ከዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የገዛ እንደሁኔታው አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ወይም የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው ዘዴ መሠረት የጉምሩክ ዋጋ ሊተመን የሚችለው፡-

   ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት በሻጩ (ዲክላራሲዮን አቅራቢዉ) እና በገዢው መካከል ግንኙነት ከሌለ ወይም ግንኙነቱ በሽያጭ ዋጋው ላይ ተጽዕኖ እንዳላሳደረ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ማስረጃ ማቅርብ ከቻለ፣

   ለ/ በገዢ በኩል ለሻጩ ከእቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ክፍያ ወይም የተሰጠ ስጦታ ከሌለ፣ እና

   ሐ/ ዕቃው በከፍተኛ ብዛት በአገር ውስጥ የተሸጠበት ነጠላ ዋጋ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት ከተቻለ ነው፡፡
4) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ቀጥሎ በተገለጹት ቀመሮች/ፎርሙላዎች መሰረት ዋጋው ይሰላል፡፡

   ሀ/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ፣ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በገባበት ሁኔታ ከተሸጠ የጉምሩክ ዋጋው እንደሚከተለው ይሰላል፡፡

   **1] DPV (Customs Value CIF in ETB) = DMP – (PFM + EXP + DTX**

   **2] FOB Price ( in USD) = DPV (CIF in USD) - IF**

   ለ/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ፣ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ከገባ በኋላ ቀጣይ የምርት ሂደት ተከናውኖበት የተሸጠ ከሆነ የጉምሩክ ዋጋው በሚከተለው ሁኔታ ይሰላል፡፡

**DPV (Customs Value CIF in ETB) = DMP – (PFM + EXP + DTX + ADD)**

**FOB Price ( in USD) = DPV (CIF in USD) - IF**

***መፍቻ***

- DPV = *የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ* (Duty Paying Value or Customs Value)
- DMP = *የሀገር ውስጥ ገበያ መሸጫ ነጠላ ዋጋ* (Domestic Market Selling Unit Price)
- PFM = *ከሽያጭ የተገኘ ኮሚሽን ወይም ትርፍ መጠን* (Commission Or Profit From Sale)
- EXP = *ሀገር ውስጥ የሚከፈሉ አጠቃላይ ወጪዎች መጠን* (Domestic General Expenses)
- DTX = *አጠቃላይ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ መጠን*(Total Customs Duties and Taxes)
- ADD = *ዕቃው ከገባ በኋላ በቀጣይ ምርት የተደረገ ተጨማሪ እሴት መጠን* (Additional value resulting from the subsequent processing of the goods)
- IF = *ዕቃው አገር ውስጥ ሳይገባ በፊት የተከፈለ የኢንሹራንስ፣ የመጓጓዣ ወጪ እና ሌሎች ወጪዎች መጠን* (Insurance, Freight and Other Costs paid up to the entry point of Ethiopia)

## 11. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም

1) የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው መሠረት ለማስላት በዕቃው ዋጋ የሚካተቱ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ክፍያዎችና ወጪዎችን ከአምራቹ ድርጅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚገኙት መረጃዎች እና ደጋፊ ማስረጃዎች በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል፣
2) በአዋጁ አንቀጽ 94 መሠረት ለመወሰን በላኪው ሀገር ተቀራራቢ የዕድገት ደረጃ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም በዕቃው ንግድ ዘርፉ አብዛኛውን ጊዜ ያለው የተለመደ ወይም አማካይ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል፡፡

## 12. ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ አፈጻጸም

የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 8 እስከ 11 የተጠቀሱትን የዋጋ ትመና ዘዴዎችን በቅደም ተከታላቸው አተረጓጎማቸውን በማስፋት በአዋጁ ከተደነገገው አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ወቅታዊ መረጃ መሰረት ከዚህ በታች በተገለጸው አግባብ በቅደም ተከተል ዋጋ ይወሰናል፡፡

1) **የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ሚዛናዊ ዘዴ፡-**

   ሀ/ በ90 ቀናት ውስጥ የገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በ180 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር የገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ለ/ ከገቢ ዕቃው ጋር በአንድ ሀገር የተመረተ አንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ በሚገኝ አገር የተመረተ አንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ሐ/ ወደኋላ በማስላት እና በወጪ ስሌት ላይ በተመሰረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት የተወሰኑ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

2) **ወደ ኋላ ማስላት ሚዛናዊ ዘዴ ፡-**

ሀ/ በብዛት የተሸጠበት ዋጋ ካልተገኘ በነጠላ የተሸጠበትን አማካኝ ዋጋ እንደመነሻ በመውሰድ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተቀመጠው ቀመር መሰረት አስፈላጊውን ተቀናሾች በመቀነስ የጉምሩክ ዋጋ ይሰላል፣

ለ/ ተጨባጭና ሊለኩ የሚችሉ መረጃዎች ማግኘት በማይችልበት ጊዜ ቀጥሎ ያሉትን ቀመሮች/ፎርሙላዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው በመጠቀም የCIF እና የFOB ዋጋን መወሰን ይቻላል፡፡

1] **DPV (Customs Value CIF in ETB) =** $\dfrac{\underline{DMP\ (1-pfm-exp)}}{1+\sum taxrates}$

**2] FOB Price ( in USD) =** **DPV (CIF in USD) - IF**

***መፍቻ:-***

- ***pfm*** = ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ የሚገኝ የትርፍ ምጣኔ በመቶኛ (*percentage rate of usual Commissions or profits from sale of such goods)*
- ***exp***= ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ ታሳቢ የሚደረግ አጠቃላይ የወጪ ምጣኔ በመቶኛ( *percentage (rate) of usual domestic general expenses in sale of such goods)*
- ***∑taxrates*** = ለዕቃው የሚከፈለው ጠቅላላ *(Cumultative Summation)* የቀረጥና ታክስ ምጣኔ ስሌት
- **CIF in USD** = CIF in ETB ሲካፈል በወቅቱ ባለው የገንዘብ ምንዛሬ መጠን

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል ለ በተመለከተው ፎርሙላ መሰረት የCIF ዋጋን ለማግኘት በገበያ ጥናት ከተገኘው የመሸጫ ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡

1] ለጅምላ ሽያጭ(አስመጪ ቀጥታ ሽያጭ) 15% እና ለችርቻሮ ሽያጭ 30% ትርፍ ተቀናሽ፣

2] ለጅምላ (አስመጪ ቀጥታ ሽያጭ) ሽያጭም ሆነ ለችርቻሮ ሽያጭ አጠቃላይ ወጪ 9%፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተመለከተው ፎርሙላ መሰረት የተገኘውን የFOB ዋጋ ከኢንቮይስ የFOB ዋጋ ለማነፃፀር ዲክላራሲዮን አቅራቢው እስከ ኢትዮጵያ ድረስ

ለኢንሹራንስ፣ ትራንስፖርት እና የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎች ስለተከፈለው መረጃ ካላቀረበ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ በቀመሩ ላይ የኢንሹራንስ ወጪ (2%)፣ የትራንስፖርት ወጪ (5%) እና የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎች (5%) በድምሩ 12% ከ**ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋው** በመቀነስ ማስላት ይቻላል፡፡

ሠ/ የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

1] ለማነፃፀሪያ የሚወሰደው ዕቃ በህጉ መሠረት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2] ዕቃው በአገር ውስጥ ሲሸጥ ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ይዘት መሆን አለበት፣ ተጨማሪ እሴት የታከለበት ከሆነ ይህንኑ መጠን በተጨባጭ ማስረጃ ሊታወቅ ይገባል፣

3] በአገር ውስጥ ሲሸጥ ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል የተደረገ ግብይት መሆን አለበት፣

4] ዕቃዎች በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጡበት የጅምላ ወይም ነጠላ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፣

5] የሽያጩ ወቅት ዕቃው በገባበት ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፣

6] በገዢው በኩል ለሻጩ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ወይም የተሰጠ ስጦታ መኖር የለበትም፡፡

7] ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዕቃው፣ ለአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የተሸጠበትን የጅምላ ወይም የችርቻሮ ዋጋ በደረሰኝ የሚያቀርብ ከሆነ እና የቀረበው ደረሰኝ በትክክል የተሸጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ ገበያ ከማጥናት ይልቅ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደመነሻ ይወሰዳል፡፡

8] ጥናቱን የሚያደርገው ቅ/ጽ/ቤት ወይም የሥራ ክፍል ዕቃው በብዛት የሚሸጥበትን ወይም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ቦታ ለይቶ ማጥናት አለበት.

9] የዕቃው ዋጋ ከፍትሃዊነት አንፃር እና ኢኮኖሚውን ያገናዘበ ቦታ ላይ የገበያ ጥናቱ ማጥናት አለበት.

10] ብዛት ያላቸው የተለያዩ አማራጭ ገበያዎች የሚገኙ ከሆነ የገበያ ጥናቱ የመጨረሻ አማካይ ውጤት ከመወሰዱ በፊት ዕቃው ቢያንስ ከሦስት ዕቃው በብዛት የሚሸጥበት ገበያ ወይም ድርጅቶች ተጠይቆ በብዛት የሚሸጥበትን አማካይ የዋጋ መረጃ መወሰድ አለበት፡፡

ረ/ የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ጥናቱን የሚያደርገው የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ 4 የተመለከቱትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ጥናቱን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

ሰ) ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ በተጠቀሰው የወደ ኋላ ሚዛናዊ ዘዴ በመጠቀም ያስተላለፈው ውሳኔ ውሳኔውን በተሰጠበት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ከዝርዝር ማስረጃዎቹ ጋር ለዳይክቶሬቱ ማሳወቅ አለበት፣

3) **በከፊል የዋጋ ማነፃፀሪያ ላልተገኘላቸው ዕቃዎች የዋጋ አወሳሰን ሁኔታ፡-**

በጉምሩክ የማነጻሪያ ዋጋ በከፊል ላልተገኘላቸው እና በሌሎች ዘዴዎች ሊተመኑ ያልቻሉ ዕቃዎች በሚከተለው ሁኔታ ዋጋ ሊወሰን ይችላል፡-

ሀ/ ባለሥልጣኑ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው የገቢ እቃዎች ዋጋን በተመለከተ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበው የዋጋ ዝርዝር በከፊል በጉምሩክ የዋጋ ማነፃፀሪያ በማይገኝበት ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከተውን ቀመር/ፎርሙላ በመጠቀም ዋጋውን ማስተካከል ወይም ማሻሻል (Uplift) ማድረግ ይቻላል፡፡

$$\text{ዋጋ ያልተገኘለት ዕቃ የጉምሩክ ዋጋ} = \frac{\text{የማነጻጸሪያ ነጠላ ዋጋ ጠቅላላ ድምር}}{\text{የኢንቮይስ ነጠላ ዋጋ ጠቅላላ ድምር}} \times \text{የዕቃው የኢንቮይስ ዋጋ}$$

መፍቻ፤

- ***ዋጋ ያልተገኘለት ዕቃ የጉምሩክ ዋጋ ማለት*** ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያስመጣቸው ዕቃዎች በጉምሩክ ማነፃፀሪያ ዋጋ ያልተገኘለትና በሌሎች ዘዴዎች መወሰን ያልተቻለ ዕቃ ማለት ነው፡፡
- ***የማነጻጸሪያ ነጠላ ዋጋ ጠቅላላ ድምር*** ማለት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ካስመጣቸው ዕቃዎች ውስጥ በጉምሩክ የተያዘው የማነጻጸሪያ ዋጋ በልጦ ለተገኘላቸው ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ድምር ነው፡፡
- ***የኢንቮይስ ነጠላ ዋጋ ጠቅላላ ድምር*** ማለት ዲክላራሲዮን አቅራቢው በጉምሩክ ካለው የዕቃዎቹ የማነጻጸሪያ ዋጋ በማነስ ለቀረቡት ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ድምር ነው፡፡
- ***የዕቃው የኢንቮይስ ዋጋ ማለት*** በጉምሩክ የማነጻጸሪያ ዋጋ ላልተገኘለት ዕቃ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበ የኢቮይስ ዋጋ ማለት ነው፡፡

ለ/ በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሠረት የሚከናወነው የዋጋ አወሳሰን ተፈጻሚ የሚሆነው ቅ/ጽ/ቤቱ ሁሉንም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ሙከራ በማድረግ ውሳኔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ ሲሆን፣ የጉምሩክ ኦፊሰሩ አግባብነት ያለውን የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ይጠቀማል፡፡

ሐ/ በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ሲደረግ፣ በማሳነስ ከቀረበው ዝርዝር አግባብነት ያለው ናሙና ለማስተካከያነት በሚወሰድበት ጊዜ የተሰጠው ውሳኔ ዋጋው ተመጣጣኝ መሆኑ ለማረጋገጥ የእቃውን ብዛት፣ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ እቃ ወይም በአንድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረቱን እቃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3(ሀ) በተገለፀው መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ሲደረግ ለማስተካከያነት የሚወሰደው የናሙና መጠን በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ከቀረበው ዝርዝር ከ10% (አስር በመቶ) ማነስ የለበትም፡፡

4) ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን፡-

ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃ ሆነው ቅ/ጽ/ቤቱ በሁሉም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በመጠቀም ውሳኔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ የዕቃውን የጉምሩክ ዋጋ ለመወሰን ዕቃው የተሠራበት የድብልቅ ንጥረ ነገሮቹ ዋጋ ተወስዶ አማካይ ሬሾ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚጨመሩ፣ ስለሚቀነሱ እና የማይካተቱ ክፍያዎችና ወጪዎች አጠቃላይ አፈጻጸም ሂደት

13. ስለተጨማሪ ክፍያዎችና ወጪዎች አፈጻጸም መርህ

በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት አለባቸው፡፡

14. ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ የሚካተቱበት ሁኔታ፣

1) በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ይካተታሉ፡-

ሀ/ በኢንቮይሱ እና ሌሎች የንግድ ሰነዶች ላይ በግልጽ የተካተቱ ስለመሆናቸው ያልተገለጸ ከሆነ፣ ወይም

ለ/ የተከፈለውም ዋጋ በትክክል ያልተቀመጠ ከሆነ፣ ወይም

ሐ/ ወደ ሀገር ከገባው ዋጋ ሊተመንበት ከቀረበው ዕቃ ጋር በተያያዘ የተከፈሉ ሲሆኑ፤ ወይም

መ/ ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበላቸው ከሆነ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ሲካተቱ፡-

ሀ/ እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈሉት ወይም የሚከፈሉት ወጪዎችና ክፍያዎች በአስመጪው እንዲቀርብ ተደርጎ ወጪው በዚያው መሠረት እንዲካተት ይደረጋል፡፡

ለ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ የቀረበው የወጪ/ክፍያ ስሌት ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በተለያየ አሳማኝ በሆነ ምክንያት መቅረብ ካልቻለ በተመሳሰይ ወቅት ከተመሳሳይ ሀገር በገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ለማጓጓዣ የተከፈለ ወጪ መሠረት ይወሰናል፡፡

ሐ/ በመልቲ ሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ከጎረቤት ሀገራት ወደቦች እስከ መድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ላለው ርቀት የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከወደብ እስከ መግቢያ ያለዉ ርቀት ከወደብ እስከ መድረሻው ካለው ርቀት ያለውን የመቶኛ ድርሻ በማስላት ይወሰዳል፡፡ ይህ ስሌት በዩኒ ሞዳል ሥርዓት ለሚገቡ ዕቃዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

መ/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በሌላ ዲክላራሲዮን አቅራቢ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የአንድ አይነት ወይም ለተመሳሳይ ዕቃ የተከፈለ ወጪ ካቀረበ በዚያ መሠረት ሊወሰንለት ይችላል፡፡

ሠ/ ለዕቃው የሚከፈለው የሮያሊቲ ክፍያ ሊሠላ የሚችለው ዕቃው ወደ ሀገር ከገባ በኋላ በሚሆን ጊዜ የመጨረሻ የዋጋ ውሳኔ ዕቃው ወደ ሀገር እስኪገባ ሊዘገይ ይችላል፡፡

ረ/ የሮያሊቲ ክፍያው በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ተጠቃሎ በአንድ ጊዜ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ የሚከፈል ከሆነ ዲክላራሲዮን አቅራቢውና ላኪው ያደረጉትን ስምምነት መሠረት ባደረገ መልኩ የቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ክፍል የዲክላራሲዮን አቅራቢዉን ጋር በመጠየቅ ተጨባጭ መረጃና ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ሚዛናዊ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

3) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች በተጨባጭና ሊለካ በሚችለው መረጃ መሠረት ሊተመኑ ካልቻሉ ባለሥልጣኑ ስለ ወጪዎችና ክፍያዎች በተመለከተ ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል መ/ቤቶች በሚገኙት ታማኝ መረጃዎችን ላይ በመመሥረት ሊተምን ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎቹ በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ በሚከተሉት ሁኔታዎች በማስላት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይካተታሉ፡-

ሀ/ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፓርት ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኝ የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ 5% (አምስት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

ለ/ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያ ወጪዎችና ክፍያዎች ዲክሌር በተደረገው የእቃው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ የ5% (አምስት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

ሐ/ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኝ የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ላይ የ2% (ሁለት በመቶ) በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 /ሀ/ እና /ሐ/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ወደ ኢትዮጵያ በአየር ተጓጉዘው ለሚመጡ ዕቃዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

15. <u>በግብይት ዋጋ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች</u>

1) ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በግብይት ዋጋ ውስጥ አይካተቱም፤

ሀ/ የፋብሪካ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች ወይም መሳሪያዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለተከናወነ ወይም ለሚከናወን የግንባታ፣ የማሻሻያ፣ የተከላ ወይም የጥገና ሥራ ወይም ለቴክኒክ ድጋፍ የሚከፈል ክፍያ፤

ለ/ ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ከገቡ በኋላ የሚከፈል የትራንስፓርት ክፍያ፤

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ ገዢው ለገባው የብድር ወይም የፋይናንስ ስምምነት የሚከፈል የወለድ ክፍያ፤

መ/ የግዢ ኮሚሽን፤

ሠ/ ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈለ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች፡፡

2) የግብይት ዋጋ ሲወሰን የሚከተሉት ክፍያዎች ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ አይደመሩም፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ የገቡትን ዕቃዎች በአገር ውስጥ እንደገና ለማምረት መብት የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

ለ) ዕቃዎቹን ለመላክ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማከፋፈል ወይም እንደገና ለመሸጥ በገዢው የሚከፈሉ ክፍያዎች፡፡

16. <u>ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች</u>

1) ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡-

ሀ/ ዕቃዎቹ በጉዞ ላይ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤

ለ/ ዕቃዎቹ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤

ሐ/ አደገኛ በመሆኑ ምክንያት እንዲቃጠል ወይም በሌላ አኳኋን እንዲወገድ የተደረገ ዕቃ ዋጋ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ 1 የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች ከዲክሌራሲዮኑ ጋር በማያያዝ እና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ለባለስልጣኑ ሲያቀረብ እና ትክክለኛነቱ በባለስልጣኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና የሌሎች ዕቃዎች የዋጋ አተማመን ሁኔታ

### 17. ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ዕቃዎች የዋጋ አተማመን ዘዴ

1) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፋያ ዋጋ በሚተመንበት ወቅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 በተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ሲሆን በጉምሩክ ተቀባይነት ባገኙ የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የአዲስ ተሽከርካሪዎች ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ወይም የአዲስ ዕቃዎች ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ በመውሰድ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ተገቢውን የእርጅና ቅናሽ በማድረግ እንዲሁም የትራንስፖርት፣ ኢንሹራንስ ክፍያና ተገቢው ተጨማሪ ወጪዎችንና ክፍያዎችን በመደመር ይሆናል፡፡ ስሌቱም በሚከተለው ቀመር/ፎርሙላ/ መሰረት ይወሰናል፡-

ያገለገለ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ዋጋ = (የአዲስ ተሽከርካሪ ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ - እርጅና ቅናሽ) H የትራንስፖርት፣ ኢንሹራንስ ክፍያ፣ ሌሎች ወጪዎችንና ክፍያዎችን ድምር

2) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ለማድረግ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ተሽከርካሪውን ወይም ዕቃውን ያገለገለ ስለመሆኑ እና ሌሎች ለዋጋ ትመና አስፈላጊ የሆኑ የዕቃው መግለጫ፣ መረጃዎችና ማስረጃዎችን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

3) ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም ሌሎች ዕቃዎች ዋጋ በሚተመንበት ወቅት ከአገልግሎት በኋላ ከኢትዮጵያ ውጭ ለተጨመሩ ዕቃዎች ወይም ለተደረጉ እድሳት የተከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች ካሉ በተጨባጭ መረጃ እና ማስረጃ በመመስረት በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት አለባቸው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች ስሌት በተጨባጭ ማስረጃ ሊወሰን ካልተቻለ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 4 ከ (ሀ)-(ሐ) በተደነገገዉ መሠረት ተቀባይነት ያገኘ የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ አዲስ ዕቃዎች ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ከእርጅና ቅናሽ በፊት በመመሥረት ይወሰናል፡፡

### 18. ያገለገለ ተሽከርካሪ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሠረት

1) የእርጅና ቅናሽን ተፈፃሚ ለማድረግ ያገለገለ የተሽከርካሪ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሠረት ተደርጎ የሚወሰደው፡-

   ሀ/ ከሌሎች የአንድ ዓይነት/ተመሳሳይ ዕቃዎች መለያ መስፈርቶች( ለምሳሌ የአንድ ሀገር ምርት መስፈርት) በተጨማሪ በምርት ዘመን፣ በሞዴል እና በሞተር ጉልበት ወይም በሲሊንደር አቅም(ሲ.ሲ) መሠረት በባለሥልጣኑ ከሚዘጋጀው የመነሻ ዋጋ ጋር በማነፃፀር ይወሰናል፡፡

ለ/ ለማነፃፀሪያ ሲባል አንድ ዓመት ወደ ፊትና ወደ ኃላ  የሆነ የምርት ዘመን ያላቸው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዓይነት ተሽከርካሪዎች በጉምሩክ ስነ ስርዓት የስራ ሂደት ሲረጋገጥ ለማነፃፀሪያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የማነፃፀሪያ ዋጋ ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በሞዴል ዓይነት ቢለይም በተመሳሳይ የአገለገለ ተሽከርካሪ የምርት ዘመን እና የሞተር ጉልበት መሠረት ይወሰናል፡፡

2 ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው  እንደተጠበቀ  ሆኖ፡-

ሀ/ ያገለገሉ የፒክአፕ፣ የሚኒባስ፣ የአውቶብስ ወይም የጭነት ተሽከርካሪዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ  የሞዴል፣ የምርት ዘመን እና የመጫን አቅምን (በሰው ብዛት ወይም በኩንታል ወይም በኪሎ ግራም) ከግምት በማስገባትና በማገናዘብ ይወሰናል፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) የተመለከተውን መረጃ ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በሞዴል ዓይነት ቢለይም በተመሳሳይ ተሽከርካሪ የምርት ዘመን እና የመጫን አቅም መሠረት ይወሰናል፡፡

ሐ/ ያገለገለ የተሳቢ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በርዝመት፣ በመጫን አቅም፣ በአክስል ብዛትና በምርት ዘመን መሰረት ይወሰናል፡

መ/ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ተሽካርካሪ ዋጋ ሲነፃፀር ተሽከርካሪው የተገጠመለት ተጨማሪ ክፍሎችና መሳሪያዎች በዋጋ ልዩነት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ግምት ውስጥ በማስገባት በተጨባጭ ማስረጃ ላይ በመመሥረት ተገቢው ማስተካከያ በማድረግ ይወሰናል፡፡

## 19. <u>ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም ዕቃዎች የእርጅና ቅናሽ አደራረግ ሥርዓት</u>

1) ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የእርጅና ተቀናሽ የሚደረገው ከታች በተገለፀው ሠንጠረዥ አንድ መሠረት የእርጅና ቅናሽ ከተሽከርካሪው የምርት ዘመን  እና አግልግሎት የሰጠ መሆኑን ከሚያስረዱ መረጃዎች በመነሳት እስከ ሦስተኛው ዓመት መጨረሻ ድረስ ከፎብ /Free on Board or FOB/ ዋጋው ላይ በየዓመቱ የሚደረግ የ10% ቅናሽ ሲሆን ከ30% አይበልጥም፡፡

ሠንጠረዥ አንድ፡- ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ በመቶኛ

| ተ.ቁ | ተሽከርካሪው ከተመረተበት ቀን ጀምሮ የቆየበት የአገልግሎት ዘመን | የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ መጠን በመቶኛ (ከፎብ ዋጋ ላይ) |
|---|---|---|
| 1 | ከአንድ ዓመት በታች (ዓመት < 1 ) | 0% |
| 2 | አንድ ዓመት እና ከሁለት ዓመት በታች (1 ≤ ዓመት <2) | 10% |
| 3 | ሁለት ዓመት እና ከሦስት ዓመት በታች (2 ≤ ዓመት < 3) | 20% |
| 4 | ሦስት ዓመት እና ከ3 ዓመት በላይ (ዓመት ≥3) | 30% |

2) በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ዲክሌር የተደረገው ገቢ እቃ ከአገለገሉ ተሽከርካሪዎች ውጭ ሌላ ያገለገለ ዕቃ ከሆነ ከፎብ ዋጋው ላይ 30% የእርጅና ቅናሽ በማድረግ እና የቀረበውን ሰነድ (ኢንቮይስ ዋጋ) በማገናዘብ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎት ወይም ጥቅም ላይ ሳይውሉ ከአንድ አመት በላይ የቆዩ ቢሆኑም የእርጅና ቅናሽ ሳይደረግባቸው አዲስ በነበሩበት ጊዜ ያለው ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት እና የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች ማደራጀት

20. የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት አደረጃጀትና አጠቃቀም

1) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የባለሥልጣኑ ኦፊሰር በዲክላራሲዮን አቅራቢዉ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋቸው ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆኑ ለማጣራት እና ተገቢውን የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ በአዋጁ መሰረት ለመወሰን የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ሲስተም ይጠቀማል፡፡

2) የዋጋ መረጃ ስርዓት በዋጋ ማጣራት ሂደት፣ በዋጋ ውሳኔ ክለሳ ሂደት፣ በድህረ-እቃ አወጣጥ ኦዲት ጊዜ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የባለሥልጣኑ ሥራዎች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ በዋጋ መረጃ ዳታቤዝ የሚገኙ መረጃዎችን የዲክላራሲዮን አቅራቢዎችን ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና ሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደረግ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ዳይሬክቶሬቱ ለገቢ ዕቃዎች ዋጋቸውን ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆናቸው ለማጣራት ለሁሉም ወይም ለተወሰኑ ዕቃዎች በስጋት ሥራ አመራር መሠረት ተቀባይነት ያለው የዋጋ ልዩነት (*permissible Deviations)* ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

5) የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት ውስጥ በመግባት የማየት፣ የመፈተሽ፣ የመጠቀም፣ የማስተካከል እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወን የሚቻለው በሚመለከተው የባለስልጣኑ ሰራተኛ ብቻ ሲሆን፤ በሚመለከተው የባለስልጣኑ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም የሥራ ክፍሉ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም የሥራ ኃላፊ ሲፈቅድ እና በመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የይለፍ ቃል ሲሰጥ ነው፡፡

6) ማንኛውም የሚመለከተው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓቱን በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ለሚፈለገው ዓላማ ብቻ መጠቀም አለበት፡፡

## 21. የመነሻ ዋጋ ስለሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች

1) በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ዋጋን ወይም የኢንቮይስ ዋጋን አሳንሶ የማቅረብ ድርጊትን ለመከላከል ሲባል ተደጋጋሚ ችግር ያለባቸው ወይም በጣም ከፍተኛ ሥጋት ያለባቸው የተወሰኑ ገቢ ዕቃዎች ላይ በባለስልጣኑ በየወቅቱ በሚዘጋጀው የመነሻ ዋጋ መሠረት በማነፃፀር የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

2) ዳይሬክቶሬቱ ከአጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በሚጣጣም መልኩ የንግድ መጠን የሌላቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች ጨምሮ ሌሎች የመነሻ ዋጋ የሚወሰንላቸው ገቢ ዕቃዎች እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

3) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በባለስልጣኑ የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ አግባብነቱ ታይቶ ሲፀድቅ ነው፡፡

## 22. ከስሪት ሀገራቸው ውጪ ከጎረቤት ሀገራት ተገዝተው የሚገቡ እቃዎችን ዋጋ ስለመወሰን

ከስሪት ሀገራቸው ውጪ ከጎረቤት ሀገራት ተገዝተው የሚገቡ እቃዎች ዋጋ ሲወሰን፡-

1) በዲክላራሲዮን አቅራቢው (በኢንቮይሱ) የቀረበው የጎረቤት አገር ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ከስሪት ሀገራቸው ተገዝተው ከገባው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በጉምሩክ የመረጃ ዋጋ ስርዓት ውስጥ የተያዘው የማነጻጸሪያ የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ሲነፃፀር እኩል ሆኖ ወይም በልጦ ከተገኘ የጎረቤት አገር ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ እንደ ሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በዲክሌራሲዮን አቅራቢው (በኢንቮይሱ) የቀረበው ኤፍ.ኦ.ቢ ዋጋ ከሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር አንሶ ከተገኘ ዕቃው የተሰራበት አገር

ሲገዛ ባለው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ መሠረት እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡

23. ***የዓለማቀፍ ዋጋ መረጃ ምንጮች ስለ መጠቀም***

*በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት ውስጥ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ማነፃፀሪያ ካልተገኘ ወይም በሚገኘው መረጃ መሠረት ውሳኔ መስጠት ካልተቻለ በሚገኙት የዓለማቀፍ ዋጋ መረጃ ምንጮችን በመመሥረት በዳይሬክቶሬቱ በሚደራጅ ወቅታዊ የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች በማነፃፀሪያነት በመጠቀም በዚህ መመሪያ በተደነገገው የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በሚጣጣም መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡*

***ምዕራፍ አምስት***

***የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ***

24. ***የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ አቀራረብ***

1) *የጉምሩክ ዋጋን በትክክል ለመወሰን እንዲቻል ዲክላራሲዮን አቅራቢው በአዋጁ አንቀጽ* 10/1/ *መሰረት የገቢ እቃዎችን አስፈላጊ መረጃዎችን በመሙላትና በማያያዝ እና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡*
2) *ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ዲክሌር በማድረግ እቃ ሲያስገባ ከዋናው የጉምሩክ ዲክለራሲዮን በተጨማሪ ከዋጋ ትመና ጋር የተገናኙ አስፈላጊ መረጃዎች በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን ውስጥ በትክክል በመሙላትና በማረጋገጥ ለሚመለከተው የባለስልጣኑ ባለሙያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡*
3) *አስፈላጊ መረጃዎችን ወደ ሲስተሙ የማስገባት ግዴታ ያለበት ዲክላራሲዮን አቅራቢ በኤሌክትሪክ፣ ሲስተም መቋረጥ ወይም በሌላ አሳማኝ አጥጋቢ ምክንያት የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን ኢሌክትሮኒክ ሲስተም በማይሰራበት ጊዜ በዋጋ መረጃ ማሳወቂያ ቅጽ/ፎርማት በመጠቀም የዋጋ መረጃን ማቅረብ ይችላል፡፡*
4) *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* 3 *መሰረት ቅጽ/ፎርማት በመጠቀም የተከናወነው ሥራ የመረጃ ስርዓቱ እንደሰራ ወዲያውኑ ወይም የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ወደ መረጃ ስርዓቱ መግባት ይኖርበታል፡፡*
5) *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* 4 *መሰረት መረጃውን ወደ መረጃ ስርዓት የማስገባት ወይም ትክክለኛነቱ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ማንኛውም አካል የመረጃ ስርዓቱ በወቅቱ መረጃውን ወደ መረጃ ስርዓቱ በአግባቡ ካላስገባ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡*

25. <u>በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን ውስጥ መካተት ያለባቸው መረጃዎች</u>

ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሚከተሉትን መረጃዎችን ጨምሮ በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡-

1) ስለ ግብይቱ የሚያስረዱ ዝርዝር መረጃዎች ፡-

ሀ/ የዲክላራሲዮን አቅራቢዉና ላኪን ጨምሮ በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ስምና ዝርዝር መረጃ

ለ/ ስለ ዕቃዎቹ የግብይት ሁኔታ፣

ሐ/ በገዢና ሻጭ መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታና ዓይነት ዝርዝር፣

መ/ የኢንቮይሱ ዋጋ፣ የምንዛሪ ዓይነት፣ የንግድ ስምምነት ዓይነት (INCOTERMS) ፣

ሠ/ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች

ረ/ ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያ

ሰ/ ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች፣

ሸ/ ከግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ ውጭ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሌሎች የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን በመተመን ለጉምሩክ ካቀረበ የተጠቀመበትን ዘዴ መግለጽ፣

2) የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መግለጫና መረጃዎች፡-

ሀ/ የዕቃው  ሙሉ ስም (የንግድ ሥም ወይም ቴክኒካል ስም)፣

ለ/ የዕቃውን አምራች ስም እና የተሰራበት አገር፣

ሐ/ የዕቃው ተጨማሪ መግለጫ ( ለምሳሌ፡- ብራንድ፣ ሞዴል ቁጥር፣ ፓርት ቁጥር፣ መጠን፣ ጉልበት)፣

መ/ ዕቃውን የተሠራበት ማቴሪያል(ከድብልቅ ማቴሪያል የተሠራ ከሆነ የይዘቱ መቶኛ መጠን)፣

ሠ/ የዕቃውን አገልግሎት(ጥቅም) መግለጫ፣

ረ/ የመድኃኒት ኬሚካል ስምና ዝርዝር ቴክኒካል መረጃ የሚያሳይ ሰነድ፣

ሰ/ የተሽከርካሪ ሥም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር (ሲሊንደር) ጉልበት፣ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እንደአስፈላጊነቱ_ ሊብሬ /የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/

ሸ/ የኤሌክትሮኒክስ፣ የማሽነሪዎችና መለዋወጫዎች ዝርዝር ማኑዋል እና ቴክኒካል ካታሎግ፣

ቀ/ የመለዋወጫ ዕቃዎች ሥም፣ የሚገጠምለት የተሽከርካሪ ዓይነት፣ የአምራች ስም፣ ኦሪጂናል ከሆነ ፓርት ቁጥሩ፣ ኦሪጂናል ካልሆነ የዕቃው አምራች ፓርት ቁጥር እና የኦርጂናል ሪፈረንስ (OEM) ፓርት ቁጥር፣

በ/ የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መግለጫና መረጃዎች፣

26. <u>ከጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን ጋር በአባሪ ስለሚቀርቡ መረጃዎችና ሰነዶች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 90 እስከ 96 በተደነገገው መሠረት የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 27 እስከ አንቀጽ 32 የተገለጹትን ዋና ዋና መረጃዎችና ሰነዶችን ጨምሮ ከዕቃ ዲክላራሲዮንና ከዋጋ መረጃ ዲክላራሱዮን ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

27. <u>በግብይት ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

በግብይት ዋጋ መሰረት ለመስተናገድ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎችና ሰነዶች እንደአስፈላጊነቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1) **ግዢ መከናወኑን የሚያሳዩ ሰነዶችና መረጃዎች፡-**

ሀ] የዋጋ ሰነድ (የሻጩ ኢንቮይስ) ፣

ለ] በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ አካላት እና ሚናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ] ገቢ ዕቃዎቹ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከመግባታቸው በፊት ዕቃዎቹን ለመግዛት የተገቡ ውሎችና ሥምምነቶች፣

መ] ከዕቃው ግዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች (ለምሳሌ፡ የአስመጪነት ፍቃድ፣ የላኪነት ፈቃድ፣ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ ፓኪንግ ሊስት፣ የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የባንክ ፈቃድና ደቢት አድቫይስ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲና ደረሰኝ፣ የማጓጓዣ ወይም ማስጫኛ ሰነድና ደረሰኝ፣

2) **ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ**

ሀ] ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

ለ] ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

ሐ] ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣

3) **ዕቃው እስከተጫነበት ወደብ ድረስ የተከፈለ ትራንስፖርትና ኢንሹራንስ ወጪ**

ሀ] ዕቃው የተላከበት (Place of export) ሀገርና ዕቃው በኮንቴነር የታሸገበት ቦታ ማስረጃ፣

ለ] ዕቃው በተላከበት ሀገር ወደብ እስኪደረስ የወጣ የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ፣

ሐ] በዕቃው ግብይት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለ ዓለም አቀፍ የንግድ ሥያሜ (INCOTERMS)

4) **ዕቃው ከተጫነበት ወደብ እስከ መጀመሪያ የኢትዮጵያ መግቢያ ድረስ የተከፈለ የውጭ ሀገር የማጓጓዣና የኢንሹራንስ ወጪ**

ሀ] የማጓጓዣ እና የኢንሹራንስ ሥምምነቱን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ] ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪዎች ማስረጃ፣

5) የኮሚሽን ክፍያ

ሀ] የውክልና ሥምምነት ሰነድ፣

ለ] የኮሚሽን ክፍያ ዓይነት የሚገልጽ ሰነድ፣

ሐ] የሻጩ ወይም የኮሚሽን ክፍያ ኢንቮይስ፣

6) የማሸጊያ እና የመያዣ ወጪ

ሀ] ዕቃውን ለማሸግ የወጣ የማቴሪያሎችም ሆነ የጉልበት ዓይነትና ወጪ፣

ለ] ዕቃውን የማሸግ ሥራው የተከናወነበት ቦታ ወይም አገር፣

ሐ] ዕቃውን የማሸግ ሥራው ያከናወነው አካል፣

መ] ከዕቃው ተነጥለው የማይታዩ የዕቃ የመያዣ ወጪ፣

7) በዲክላራሲዮን አቅራቢው ለላኪው የቀረቡ ግብዓቶችና አገልግሎቶች

ሀ] ዕቃውን ለማግኘት ወይም ለማምረት በገዢው በቀጥታ ወይም በገዢው ሥም በሦስተኛ ወገን በኩል ለአምራቹም ሆነ ለላኪው የቀረቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር፣

ለ] ከላይ የተጠቀሱት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማምረቻ ወጪ ወይም የግዢ ዋጋ እና የማድረሻ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

8) የሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች

ሀ] በዕቃው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን አካላት ሚናና ግንኙነት የሚያስረዳ መግለጫ፣

ለ] የሮያሊቲና ፈቃድ ሥምምነት ሰነድ፣

ሐ] የሽያጭ ሥምምነት ሰነድ፣

መ] ከዕቃው ገዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

9) መልሶ ከመሸጥ ከሚገኘው ገቢ ላይ የሚከፈሉ ክፍያዎች

ሀ] የሽያጭ ሥምምነት ሰነድ፣

ለ] ገዢው ዕቃው መልሶ በመሸጥ፣ በሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሐ] ከዕቃው ገዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

10) ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ

ሀ] የዕቃዎች ወይም የአገልገሎቶች ግዢ ውል ሰነድ፣

ለ] ክፍያዎቹ ዕቃዎቹ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለወጡ ወጪዎች የተከፈሉ መሆናቸውን የሚያሳይ መግለጫ፣

ሐ] የተደረገው/የሚደረገው ድጋፍ ዓይነትና ወጪ መጠን ማስረጃ፣

መ] ወጪዎቹ ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

*11) ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተከፈሉ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪዎች*

ሀ] ዕቃዎች ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የወጣ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪ መኖሩን የሚያሳይ መግለጫ፣

ለ] የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪው መጠን፣

ሐ] የአገልግሎቱ ባህሪና ሁኔታ፣

መ] ወጪው በዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተቱን ወይም አለመካተቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣

12) **ተቀናሽ የፋይናንስ ወጪዎች፤**

ሀ] ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡት እቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ በገዢው የተከፈለውን የብድር ወይም የፋይናንስ ወለድ ክፍያና የክፍያ ስምምነት ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ] ክፍያውን ዘግይቶ እንዲፈፀም የሚያስችሉ ሥምምነቶች የሚያስረዳ ሰነድ፣

13) **ግንኙነት(ዝምድና) ያላቸው አካላት፣**

ሀ] በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት ሁኔታና ዓይነት፣

ለ] በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት በዕቃው ግብይት ዋጋ ላይ ያለው ተፅዕኖ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ፣

ሐ] የኮርፖሬቱ(ድርጅቱ) ዝርዝር ፕሮፋይልና የዋጋ ፖሊሲ የሚያሳይ ሰነድ፣

መ] የገዢውን የማከፋፈል ወይም የኤጀንት(ብቸኛ ወኪል) መብት ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣

ሠ] የዕቃው የሽያጭ የውል ሰነድ እና የሻጩ ኢንቮይስ፣

ረ] በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል የተከናወነ ሽያጭ (ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ) አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

ሸ] ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች፣

28. <u>የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡ ነጠላ ዋጋ (Unit Price) የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎች ማስረጃ፣
4) የአንድ አይነት ዕቃዎች የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ(Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

29. <u>የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡ ነጠላ ዋጋ (Unit Price) የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎች ማስረጃ፣
4) የተመሳሳይ ዕቃዎች የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ (Price List) የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

30. <u>ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ዋጋን ለመተመን መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) በሻጩ (ዲክላራሲዮን አቅራቢው) እና በገዢው (አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ነጋዴ) መካከል ያለው የዝምድና ሁኔታ እና በእቃው የሀገር ውስጥ መሸጫ ዋጋ ላይ ያለው ተጽእኖ የሚያስረዳ ማስረጃ ፣
3) የሽያጩ ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎችና ማስረጃዎች፣
4) የሻጩ (ዲክላራሲዮን አቅራቢው) ዕቃዎችን የሚሸጥበት ዋጋ ዝርዝር ማስረጃ፣
5) የሽያጭ የውል ሰነድ ወይም ኢንቮይስ እና ክፍያ የተፈጸመበት ማስረጃ፣

31. <u>የዕቃውን ጉምሩክ ዋጋ በወደ ኋላ ማስላት ዘዴ ለማስላት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች</u>፡-

1) የዕቃው ወይም የአንድ ዓይነት/ተመሳሳይ ዕቃ የመሸጫ ዋጋ፣ የሽያጭ ወጪና ትርፍ ማስረጃ፣
2) ከዕቃው ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ የወጡ ወጪዎችና ክፍያዎች ዝርዝር፣
3) ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከመሸጡ በፊት የተከናወነ ቀጣይ የምርት ሂደት ካለ ያስከተለው ተጨማሪ እሴት መጠን የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣
4) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የሚከፈሉ የቀረጥና ታክስ መጠን፣
5) የዕቃው የንግድ ዘርፉን አማካይ የኮሚሽን ወይም የትርፍ ምጣኔ፣ የወጪዎች ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣
6) የዕቃው የንግድ ዘርፉን አማካይ የማጓጓዣ፣የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣

32. <u>በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች</u>

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣
2) ዕቃዎቹ በላኪው የተመረቱና የተላኩ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣
3) በላኪው ሀገር ዕቃዎቹን ለማምረት የወጣውን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣
4) በላኪው ሀገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም የእቃውን ንግድ ዘርፉን አብዛኛውን ጊዜ ያለው (የተለመደ ወይም አማካይ) የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ፣
5) ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ማስረጃ፣
6) ለዕቃዎቹ የወጣ ሌሎች ክፍያዎችና ወጪዎች የሚያሳይ ማስረጃ፣

33. <u>ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ዋጋን መወሰን መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች፣</u>

1) በዚህ ዘዴ መሠረት የዕቃውን ዋጋ መተመን ትክክል የሚሆንበት ምክንያት የሚያሳይ ማስረጃ፣
2) በዚህ ዘዴ መሠረት የዕቃውን ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ሰነዶች፣

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የጉምሩክ ዋጋ ትመና የሚያከናውኑ አካላት ወይም ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የዳይሬክቶሬቱ፣ የሥራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

34. <u>የዳይሬክቶሬቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ዳይሬክቶሬቱ በባለሥልጣኑ ከተሰጠው ሌሎች የሥራ ኃላፊነቶችና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል፦

1) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓትን ማልማት፣ ማሻሻልና ማስተዳደር፣
2) በባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ የዋጋ መረጃዎችን እና ከሌሎች በዓለማአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸው የዋጋ መረጃ ምንጮች የዋጋ መረጃ መሰብሰብ እና መተንተን፤ የተተነተነውን የዋጋ መረጃ ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ ማዘጋጀት ወይም ማደራጀት፤ በዋጋ መረጃ ስርዓቱ የሚገኝ መረጃን ተገቢው ማስተካከያ ማድረግ እና በየጊዜው የዋጋ መረጃ ስርዓቱ ወቅታዊ በማድረግ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተደራሽ እንዲሆን እና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

3) በዋጋ አተማመን ዙሪያ የአሰራር ማኑዋል ማዘጋጀት፣ በዋጋ አተማመን ዙሪያ በአዋጅ፣ በመመሪያው በተደነገገው መሠረት እንዲሁም በተዘረጉ አሰራሮች መሠረት በባለስልጣኑ ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ፣

4) ባለስልጣኑን ወክሎ በዋጋ አተማመን ዙሪያ ከተጓዳኝ መ/ቤቶች እና ከሌሎች ሀገራትና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግኑኝነት በመፍጠር የሚገኙ ልሞዶችን በማዳበር አስፈላጊ የሆኖ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በአገራችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

5) ሁሉም የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ እና ተመሳሳይ የዋጋ አተማመን ሥርዓት እየተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

6) ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ከሌሎች ክፍሎች በዋጋ ትመና የአሠራር ሥርዓት ዙርያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ምላሽ መስጠት፤

7) ዳይሬክቶሬቱ ከሚያገኘው መረጃዎችና ከሚቀርብለት ሪፖርቶች በመነሳት ሳይሰበሰብ የቀረ ቀረጥና ታክስ ካለ አጣርቶ በሚመለከተው ቅ/ጽ/ቤት የድህረ እቃ አወጣጥ የስራ ሂደት/ክፍል አማካይነት እንዲሰበስብ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ እና ድጋፍ መስጠት፣

8) በዋጋ አተማመን የአሰራር ስርአት ዙርያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለተቋሙ ሰራተኞችና ለሚመለከታቸው አካላት መስጠት፣

9) ሌሎች ከዋጋ ትመና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት መፈጸም፡፡

35. <u>የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በባለሥልጣኑ ከተሰጠው ሌሎች የሥራ ኃላፊነቶችና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) እና ኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ማቅረቢያ ዲክሌራሲዮን (VDD) እና ተያያዥ የጉምሩክ ዳታቤዝ ሥርዓቶች በተመለከተ፣

   ሀ/ ዘመናዊ፣ ጥራት ያለው እና ለአጠቃቀም ቀላል እንዲሆን በየጊዜው በመፈተሸ ተገቢው ማሻሻያ ያደርጋል፣

   ለ/ አገልግሎቱ ሳይቋረጥ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል፣

   ሐ/ የአጠቃቀሙን ሁኔታ በመገምገም ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመወያየት አስፈላጊው ማሻሻያ ያደርጋል፣

2) የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ሥርዓትን እና ተያያዥ የጉምሩክ ዳታቤዝ ሥርዓቶች የአጠቃቀም ዝርዝር የአፈጻፀም ማንዋል መሠረት በሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ፈቃድ ያገኙ የሚመለከታቸው ሠራተኞችን በመለየት፣ የመጠቀሚያ መለያና

የይለፍ ቃል (ፓስዎርድ) መስጠትና መሰረዝ፣ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት እና መቆጣጠር፣

3) ከብሔራዊ ባንክ የሚላከውን ሳምንታዊ የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመቀበል በአሲኩዳ ሲስተም ውስጥ በማስገባት በባለስልጣኑ ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያሳውቃል፡፡
4) በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት አጠቃቀም ዙርያ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመተባበር ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎችና ቅ/ጽ/ቤቶች ስልጠናና አስፈላጊው ድጋፍ መስጠት፣
5) ከዳይሬክቶሬቱ ጋር አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ሥርአት በመዘርጋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣
6) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመረጃ ስርዓቱ የአጠቃቀም ሪፖርቶችን በማውጣት ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መስጠት

36. <u>የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ሃላፊነት</u>

ሁሉም የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ሌሎች በባለሥልጣኑ የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነትና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናሉ፡-

1) በባለሥልጣኑ የሚወጡ የዋጋ አተማመን መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራር ሥርዓቶች እንዲሁም የፕሮሲጀር ማንዋሎች በትክክል ሥራ ላይ ማዋልና እንዲውሉ ማድረግ፣
2) በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ በወጥነት እና በትክክል ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣
3) ለዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ በግብአት የሚያገለግሉ መረጃዎች እና ከዋጋ መረጃ ዳታቤዝ ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በጥራትና በአግባቡ እንዲመዘገቡ/እንዲደራጁ/ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በየጊዜው ለዳይሬክቶሬቱ ማስተላለፍ፣
4) በቅ/ጽ/ቤቱ ደረጃ ለሚቀርቡ የዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ትመና የሥራ ክፍል በኩል አግባብነት ያላቸውን የዋጋ መረጃ ምንጮች በማገናዘብ ወጥነት ባለው መልኩ ተገቢው ምላሽ እንዲሰጣቸው ማድረግ፣
5) በቅ/ጽ/ቤቱ ለሚገኝ የዋጋ ትመና የሥራ ክፍል የሚቀርቡ ከዋጋ አተማመን አሠራር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ከቅ/ጽ/ቤቱ አቅም በላይ ሲሆኑ ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመነጋገር ጥያቄውን ላቀረበው አካል ምላሽ መስጠት፣
6) በቅ/ጽ/ቤቱ ለሚገኝ የዋጋ ትመና የሥራ ክፍል በተለያየ ጊዜ ለሚቀርቡ የዋጋ እና ከዋጋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ቡድኑ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ለዳይሬክቶሬቱና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፣
7) በቀጥታ በኔትዎርክ ያልተገናኙ የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኙ ዋጋዎችን በማጠናቀርና በኤክሴል ፎርማት በማዘጋጀት በየወሩ መጨረሻ ለዳይሬክቶሬቱ መላክ፤

8) በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኝ የዋጋ ትመና የሥራ ክፍል ባስተላለፋቸው ውሳኔዎች ላይ ጥያቄዎች ሲቀርቡ እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከተው አካላት ማብራሪያ መስጠት፣

9) በባለሥልጣኑ ደረጃ በሚዘጋጀው ዝርዝር የአፈጻፀም ማንዋል መሠረት በአግባቡ መሥራት፣

10) ሌሎች በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ መፈፀም ያለባቸው ዋጋ ትመናን የተመለከቱ ሥራዎች ማከናወን ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ የጉምሩክ ኦፊሰሮች ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 37. የጉምሩክ ኦፊሰሮች የዋጋ ማጣራት እና የመወሰን ስልጣን

1) የሰነድ ማረካከቢያና ማረጋገጫ ኦፊሰር (የፌስቬት ኦፊሰር) አንድ ዲክለራሲዮን ዲክሌር ተደርጎ ለባለስልጣኑ ሲቀርብ የቀረበውን ዲክለራሲዮን የተሟላ ሰነድ በማረጋገጥ ይረከባል፤ዲክለራሲዮኑ በባለስልጣኑ ካለው የስጋት ደረጃ አንጻር አጣርቶ ለቀጣይ ስራ ለሚመለከተው ኦፊሰር ያስተላልፋል፡፡

2) በቅ/ጽ/ቤቱ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በየደረጃው በማንኛውም ጊዜ የዋጋ ማጣራት ሥራዎችን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

3) የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልቶ ዲክሌር በተደረገውና በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀረበው ዲክለራሲዮን ላይ ተዘርዝረው የሚቀርቡ እቃዎች ዋጋ የሚጣራውና ውሳኔ የሚሰጠው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሠረት ዲክሌር በተደረገው የዋጋ መጠን እና የሥራ ኃላፊነት ደረጃ መሠረት ይሆናል፣

4) በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጉምሩክ ኦፊሰሮች በየደረጃቸው የሚከተሉት የማጣራት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡-

ሀ/ በአንድ ዲክለራሲዮን ውስጥ ዲክሌር ተደርጎ በቀረበው ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ያልበለጠ የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ያላቸው ገቢ ዕቃዎች በሠነድ ምርመራ ኦፊሰር ወይም በሌላ የሚመለከተው ኦፊሰር የሚጣሩና ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል፤

ለ/ በአንድ ዲክለራሲዮን ውስጥ ዲክሌር ተደርጎ ከቀረበው ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) በላይ የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ያላቸው ገቢ ዕቃዎች በሠነድ ምርመራ ከፍተኛ ኦፊሰር ወይም በሌላ የሚመለከተው ከፍተኛ ኦፊሰር የሚጣሩና ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋጋቸው አነስተኛ የሆነ ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በታች የሆኑ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋቸው ለመወሰን በጣም አስቸጋሪ መሆናቸው በሚታመንበት ጊዜ የሥራ ክፍሉ

ኃላፊ በከፍተኛ ኦፊሰር ወይም ከዛ በላይ ባለው ባለሙያ በኩል ተጣርቶ እንዲወሰን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

መ/ የባለሥልጣኑ የአቤቱታ አጣሪ ቡድን አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4(ሀ) እና (ለ) በተሰጡ የዋጋ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታዎች ሲቀርቡ በቅድሚያ በሥራ ክፍሉ የቅርብ ኃላፊ ታይቶ የቡድኑ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ምርምራ ኦፊሰሮች ወይም ከፍተኛ ኦፊሰሮች ወይም የዕቃ አወጣጥ ቡድን አስተባባሪ ከዋጋ ትመና ጋር በተያይዞ ውሳኔ ሲሰጡ የዋጋ ትመና ሥራ ክፍልን ወይም የቅ/ጽ/ቤቱ የሚመለከተው ኃላፊን በመጠየቅ አስፈላጊውን ድጋፍ ያገኛሉ፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት የዕቃው ዋጋ ለመተመን የሚያስችሉ ሁኔታዎች ወይም ዋጋውን ለመወሰን ተጨማሪ መረጃ በሚያስፈልግ ጊዜ በቀጥታ ለዋጋ ትመና ሥራ ክፍል እንዲተላለፍ በማድረግ በዋጋ ትመና የሥራ ክፍሉ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

38. <u>የጉምሩክ ኦፊሰር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የሚመለከተው የጉምሩክ ኦፊሰር በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የዕቃውን ዋጋ የመተመን እና ቀረጥና ታክስ የማስላት ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

2) የጉምሩክ ኦፊሰሩ በቀረበው ዋጋ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ካደረበት የዋጋ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን ሁሉ አሟጦ በመጠቀም ውሳኔ መስጠት እንዲችል ከዲክላራሲዮን አቅራቢው ተጨማሪ መረጃና ሰነድ መጠየቅ አለበት ፡፡

3) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በጉምሩክ ኦፊሰር የተጠየቀውን ተጨማሪ መረጃና ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ ወይም ምላሽ ካልሰጠ፣ ኦፊሰሩ የእቃዎቹን ዋጋ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ባሳወቀው መሠረት መተመን እንደማይቻል በመግለጽ የሚኖረው ቀጣይ ውሳኔ በተመለከተ መረጃው በቀረበው በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

39. <u>የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ስለ ማድረግ</u>

1) በአዋጁ ውስጥ ስለ ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ከተደነገገው አንጻር በሚደግፍና በሚጣጣም መልኩ በተመረጡት ጉዳዮች ላይ ወይም ከፍተኛ ሥጋት ባለባቸው ዕቃዎች ላይ በማተኮር የተሰጠው የዋጋ ውሳኔ በአዋጅ፣ በመመሪያና በአሠራር መሰረት በአግባቡ ስለመከናወኑ በቅ/ጽ/ቤት እና በዋ/መ/ቤት ደረጃ በሚቋቋመው የክለሳ ኮሚቴ በኩል የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ይደረጋል፡፡

2) የቅ/ጽ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ከዕቃ አወጣጥ ቡድን፣ ከልዩነት አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቡድን፣ ከዋጋ ትመና ቡድን እና ከድህረ-እቃ አወጣጥ የሥራ ሂደት የተውጣጡ ቢያንስ አራት ባለሙያዎች ይኖሩታል፡፡

3) የቅ/ጽ/ቤቱ የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ለክለሳው ሥራ መነሻዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ/ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የተሰጠው የዋጋ ውሳኔ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ በሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም በሥራ ሂደት በኩል በቀረበ አስተያየት፣

ለ/ ከዋ/መ/ቤት የዋጋ ማጣራት ክለሳ ኮሚቴ በቀረበ አቅጣጫ/መረጃ/፣

ሐ/ በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ከፍተኛ ሥጋት ያለባቸውና ተደጋጋሚ ቅሬታ በሚቀርብባቸው ዕቃዎች ላይ የተሰጠ የዋጋ ውሳኔን በተመለከተ፣ ወይም

መ/ ኮሚቴው ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በሚያገኘው ግብአት በመጠቀም የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ያደርጋል፡፡

4) የቅ/ጽ/ቤቶች የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴዎች የሚያስተላልፏቸው የዋጋ ውሳኔዎች በሙሉ ዋናው መ/ቤት ወደ የሚገኘው የዋጋ ክለሳ ኮሚቴ እና ለዳይሬክቶሬቱ መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

5) የዋናው መ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጉምሩክ ፕሮግራምና ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ ሆኖ ከዳይሬክቶሬቱ፣ ከህግ ተገዥነትና ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ ከድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት፣ ከጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እና ከጉምሩክ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት የተውጣጡ ቢያንስ አምስት ባለሙያዎች ያካተተ አባላት ይኖሩታል፡፡

6) የዋና መ/ቤት የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴ ለክለሳው ሥራ መነሻዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ/ በቅ/ጽ/ቤቶች ወይም በዳይሬክቶሬቱ ደረጃ የተሰጠው የዋጋ ውሳኔ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጉምሩክ ፕሮግራምና ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት፣

ለ/ ከቅ/ጽ/ቤቶች የዋጋ ማጣራት ክለሳ ኮሚቴ በቀረበ ሪፖርትና ውሳኔዎች፣

ሐ/ በሥጋት ሥራ አመራር መርህ መሠረት ከፍተኛ ሥጋት ያለባቸውና ተደጋጋሚ ቅሬታ በሚቀርብባቸው ዕቃዎች ላይ የተሰጠ የዋጋ ውሳኔን በተመለከተ፣ ወይም

መ/ ኮሚቴው ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በሚያገኘው ግብአት በመጠቀም የዋጋ ውሳኔ ክለሳ ያደርጋል፡፡

7) ዳይሬክቶሬቱ ከዋናው መ/ቤት የዋጋ ክለሳ ኮሚቴ የሚላኩለትን ሰነዶች በመመርመርና እንዲሁም በማደራጀት ለኮሚቴው ሥራ እገዛ ያደርጋል፡፡

8) በዚህ አንቀጽ መሠረት በዋጋ ውሳኔ ክለሳ ኮሚቴዎች በኩል በተደረገው ማጣራት በተገኙት ግኝቶች መሠረት ቀሪ ሂሳብ ካለ ለሚመለከተው የቅ/ጽ/ቤት የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ክፍል በማስተላለፍ ቀጣይ ዝርዝር ማጣራት ተደርጎ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

9) ኮሚቴዎቹ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ለዘርፉ በማሳወቅ ከዚህ መመሪያ በሚጣጣም አግባብ የውስጥ አሠራራቸውን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን በጋራ ወስነው ተግባራዊ ሊያደረጉ ይችላሉ፡፡

10) የዋጋ ክለሳ ሥራ የዕቃው ዲክሌራሲዮን በፌዝቬት ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ እስከ 5/አምስት/ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የዲክላራሲዮን አቅራቢው ግዴታዎች እና መብቶች

### 40. የዲክላራሲዮን አቅራቢው ግዴታዎች

ዲክላራሲዮን አቅራቢው፡-

1) በጉምሩክ አዋጅና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክሌራሲዮን እና ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ ከሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፡፡

2) የዕቃው የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክለራሲዮን በሚያቀርብበት ጊዜ፡-

ሀ/ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ ከገቢ ዕቃዎቹ ዋጋ አተማመን ጋር ግንኙነት ያላቸው ዝርዝር መረጃዎችና ሰነዶች ማቅረብ አለበት፣

ለ/ በባለሥልጣኑ በኩል በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚዘጋጁ ቅጾች ወይም ሰነዶች ላይ መረጃ በአግባቡ በመሙላት ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ ለባለሥልጣኑ በሚያቀርባቸው ዲክሌራሲዮን፣ መረጃዎች እና ደጋፊ ሰነዶች ትክክለኛነት ላይ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፤ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በፊርማው በማረጋገጥ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፡፡

3) በዕቃው ዲክላራሲዮን ውስጥ ለሰፈሩት ዝርዝሮች እና ደጋፊ ሰነዶችና መረጃዎች መሟላትና ትክክለኛነት በአዋጁ መሰረት ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

### 41. የዲክላራሲዮን አቅራቢዉ መብቶች

1) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በባለሥልጣኑ ወይም በጉምሩክ ኦፊሰር የተሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ የማወቅ መብት አለው፡፡

2) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በባለስልጣኑ መ/ቤት በሚመለከተው የጉምሩክ ኦፊሰር በሚወስነው የቀረጥና ታክስ መጠን መሰረት ለአምራች የኢንሹራንስ ዋስትና፣ ለመንግስት መስሪያ ቤት የጹሁፍ/ ዋስትና እና ለሌላ ዲክላራሲዮን አቅራቢ የጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ ጋራንቲ በማስያዝ ዕቃውን ማስለቀቅ ይችላል፡፡

3) ከዋጋ ትመና ጋር በተያያዘ ዋስትና በማስያዝ ዕቃውን ማስለቀቅ የሚችልባቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው፡፡

ሀ/ በዚህ መመሪያ መሠረት ዋጋን ለመተመን የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎች በበቂ ምክንያት ያልተሟሉ ሲሆንና እነዚህ ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ፣

ለ/ የዕቃዎችን ዋጋ በአጭር ጊዜ በማጣራት ተገቢው ውሳኔ ማስተላለፍ በማይቻልበት ጊዜ፣

ሐ/ በዋጋ አተማመን ረገድ በዲክላራሲዮን አቅራቢው እና በባለሥልጣኑ መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት የመጨረሻ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈለባቸው በዋስትና እንዲለቀቁ ለማድረግ፤

4) በባለስልጣኑ በተሰጠው የዋጋ ውሳኔ ላይ ያልተስማማ የዲክላራሲዮን አቅራቢ በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች ውስጥ በተደነገገው መሠረት አቤቱታው ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ወይም አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ሌሎች ድንጋጌዎች

### 42. የገንዘብ ምንዛሪ

1) የገንዘብ ምንዛሪን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 101 በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየሳምንቱ ረቡዕ ከብሔራዊ ባንክ የሚላከውን ሳምንታዊ የምንዛሬ መጠን በመቀበል በአሲኩዳ ሲስተም ውስጥ በማስገባትና በማሻሻል በባለስልጣኑ ደረጃ ከሐሙስ ጀምሮ እስከሚቀጥለው ሳምንት ድረስ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤ እንዲሁም ለዳይሬክቶሬቱ፣ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት በፅሑፍ ያሳውቃል፡፡

### 43. ልዩ የዋጋ መስተንግዶ ሁኔታ

1) ባለሰልጣኑ ሲፈቅድ ከታች የተዘረዘሩት ዲክራሲዮን አቅራቢዎች በድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በኩል ማጣራት ተደርጎ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ በክሊራንስ ጊዜ በሰነዳቸው ባቀረቡት የግብይት ዋጋ መሠረት በቀጥታ ሊስተናገዱ ይችላሉ፤

ሀ/ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ዕቃዎች ሲያመጡ፣

ለ/ አምራች ወይም የሁለተኛ መደብ የጉምሩክ ታሪፍ ተጠቃሚዎች ለግብአት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎች እና ሌሎች ለምርት አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ሲያመጡ፣

ሐ/ በባለሥልጣኑ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ/AEO/ አስመጪዎች ዕቃዎች ሲያመጡ፣

መ/ በኢንቨስትመንት ፈቃድ በቀረጥ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች፣

ሠ/ የመንግስት ፕሮጀክቶች ለመሥራት በግል ድርጅቶች የሚገቡ ዕቃዎች፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተደነገገው በተጨማሪ በሥጋት ሥራ አመራር አሠራር መሠረት ተጣርቶ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለውን ዕቃ ዋጋው በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት ውስጥ ከተያዘው ዋጋ ጋር ያለው ልዩነት ከ10 በመቶ የበለጠ ቢሆንም ለሚመለከተው የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ስራ ክፍል በማሳወቅ ቀጣይ የማጣራት ሂደት እና ቀሪ ሂሳብ ካለም የመጠየቅ ሂደት እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሰነዱ ባቀረበው ዋጋ መሠረት በቀጥታ ሊያስተናገድ ይችላል፡፡

3) ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሠረት የሰጠውን መስተንግዶ የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት በየ15 ቀኑ ለቅ/ጽ/ቤቱ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ክፍል እና ለዳይሬክቶሬቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

44. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጐች</u>

1) የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006 እና ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ ይሰራባቸው የነበሩ ልምዶችና አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ብቻ የሲዲ አሰራር ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

45. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነባሩ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

46. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ -----------------------ቀን 2008 ዓ.ም

በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር